**«ስብእናዋን ሸጣ ከመኖር መታሰርን አይደለም መሞትን መረጠች !**

ግርማ ካሳ
muziky68@yahoo.com

የካቲት 26 2001

ታሪኩ እንደዚህ ነዉ። የአንድ ከፍተኛ የግብጽ ባለሥልጣን ቤት ዉስጥ አገልጋይ ሆኖ አንድ ወጣት ይሰራል። ባለሥልጣኑ ይህንን አገልጋይ በጣም ያምነዉና ያከብረዉ ስለነበረ በቤቱ ላይ ትልቅ ኃላፊነት ሰጠዉ። በቅንነትና በእዉነት በዚህ ባለሥልጣን ቤት እየሰራና እያገለገለ ባለበት ወቅት አንድ የተለየ ችግር ተፈጠረ።

ባለሥልጣኑ በሥራ ምክንያት ለረጅም ጊዜ ከከተማዉ ርቆ በሄደ ጊዜ የባለሥልጣኑ ባላቤት አይኗን በዚህ በታማኝ አገልጋይ ላይ ጣለች። በድብቅ ማንም ሳያዉቅ የማይገባ ነገር ማድረግ ፈለገች። ታማኙ አገልጋይ ግን «እነሆ ጌታዬ በቤቱ ያለዉን ምንም የሚያወቀዉ የለም። ያለዉንም ሁሉ ለኔ አስረክቦኛል። ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰዉ የለም። ሚስቱ ስለሆንሽ ከአንቺ በቀር በቀር ያልሰጠን ነገር የለም። እንዴት ታዲይ ይሄን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ ? በእግዚአብሄር ፊት እንዴት ሐጢያት እሰራለሁ ? » ሲል መለሰላት።

ታማኙ አገልጋይ ከሚያምንበትና ከሚከተለዉ መርህ ዉጭ ተገቢ ያልሆነ ሥራ እንዲሰራ በባለስልጣኑ ሚስት ማስፈራራትና ዛቻ እየተደጋገመ ደረሰበት።

አንድ ጊዜ ሥራዉን ሊሰራ ወደ ቤቱ ሲገባ ለብቻዉ አገኘችዉ። ልብሱን ይዛ፣ ላዩ ላይ ተጠመጠመች። ታምኙ አገልጋይ ግን ልብሱን ትቶ ወደ ዉጭ ሸሸ። የባለሥልጣኑ ሚስት ተበሳጨች። ተቆጣች። «እንዴት ይንቀኛል፣ እንዴት የምጠይቀዉን አይሰማም» ብላ ልታሲዘዉ ጩኸቷን አቀለጠችዉ። ዘበኞች ተሯሩጠዉ ከዉጭ ሲመጡ « ሊደፍረኝ ነበር። ይኸዉ ስታገለዉና ስጮህ ደንግጦ ልብሱን እኔ ዘንድ ጥሎ ሸሽቶ ሄደ» ብላ በዉሸት ወነጀለቸዉ።

እዉነቱ ሌላ ነበር። ነገር ግን እልህ ንዴት በቀልና «እኔ ያልኩትን ለምን አልሰማም፣ እንዴት ይንቀኛል» የሚል በስልጣን የመመካት ነገር ስለነበር እዉነት ተረግጦ፣ ሳያጠፋ ጥፋተኛ፣ ሳይዋሽ ዉሸታም፣ ቅን በሰራ ወንጀለኛ ተብሎ ይህ ታማኙ ወጣት አገልጋይ ወህኒ ወረደ።

ይህ ወጣት ከአራት ሺህ አመት በፊት ይኖር የነበረ፣ በመጽሃፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰዉ የአብርሃም የልጅ ልጅ የይስዓቅ ልጅ የሆነዉ ያዕቆብ ከወላዳቸዉ አሥራ ሁለት ወንድ ልጆች መካከል አንዱ ዮሴፍ ነበር።

በዉሸትና በእልህ ያኔ ዮሴፍ እሥር ቤት እንደወረደዉ ሁሉ አሁንም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳም እሥር ቤት በግፍና በዉሸት ቃሊቲ ወርዳለች።

ወንጀሏ ምን ቢሆን ነዉ? ምን ይሆን ያጠፋችዉ? የትኛዉን የሕግ አንቀጽ ነዉ የተላለፈቸዉ ? የት ቦታ ነዉ የሰዉ ደም ያፈሰሰቸዉ ? መቼ ነዉ የጥላቻና የአመጽ ፖለቲካን ያስፋፋቸዉ ? «ቅንጅት የሰዉ ጠላት የለዉም፣ በጠመንጃ ችግርን ለመፍታት መሞከር የኋላ ቀርነት ነዉ » ማለቷ ነዉ ችግር የፈጠረዉ ? በአገር ሽማግሌ ወግና ስርዓት ለእርቅና አለሰላም ስል ይቅርታ ጠይቂያለሁ ማለቷ ነዉ ስህተቱ ?

እነ አቶ ገበየሁ ወርቅነህ «ያልሆነዉን ሆነ፤ ያልተባለዉን ተባለ፤ ያልተሰራዉን ተሰራ» ብላ እንድትዋሽ አስጠነቀቋት። ዛቱባት። በሕዝብ ገንዘብ የሚተዳደሩና የሁሉንም አቋም በእኩልነት ማስተናገድ የነበረባቸዉ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ረድዮ ሃላፊነታቸዉን ጥለዉ ርካሽ የገዢዉ ፓርቲ ፕሮፖጋንዳ መሳሪያ በመሆን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ ተከታታይ የስም ማጥፋትና የማስፈራራት ዘመቻ ለቀናት አደረጉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ቃሌ» በሚለዉ ጽሁፏ እዉነትን ተናገረች። ከአንድ አመት ተኩል በፊት መጀመሪያ ከታሰረችበት እሥር ቤት የተፈታቸዉ በአገር ሽምግልናና ወግ መሰረት ይቅርታ ጠይቃ እንደሆነ አስረዳች። ነገር ግን የሕወሃት ባለሥልጣናት እዉነት አልዋጥላቸዉ አለ። እነርሱ መዋሸትና ማጭበርበር እንደለመዱት ልማዳቸዉ ነዉና ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንድትዋሽና እንድታጭበረብር ፈለጉ። እነርሱ እንደቀለሉት እርሷም እንድትቀል ፈለጉ።

ወ/ት ብርትካን «እምቢ» አለች። ለእዉነት ቆመች። እነርሱ አስፈራሯት። በሚቆጣጠሩት ሬዲዮና ቴሌቭዥን ዛቱባት። እርሷም «ፍንክች አልል» አለች። ቁርጠኝነት ይሉታል ይሄ ነዉ።፡

በመጨረሻ በአሥር ወጠምሻ እንሥሶች በቁጥጥር ሥር እንድትወል ተደረገ። ባላጠፋቸዉ ጥፋት «ለምን እዉነትን ተናገርች» ተብላ ቃሊቲ ወረደች። በቴሌቭዥንና በሬዲዮ የዉሸት ክስ ተደረደረባት። ጥፋተኛ እንደሆነች ነጭ ከጡር እያጋጩ ሊያሳምኑ ሞከሩ።

እዉነት ግን እዉነት ናት። የኢትዮጵያ ህዝብና የአለሙ ሕብረተሰብ  እዉነት ማን ጋር እንዳለች ያወቃል። የአገር ሽማግሌዎች ምንም እንኳን አሳዛኝና አሳፋሪ በሆነ መልኩ ዝምታን ቢመርጡም እዉነቱን ያወቃሉ። በርካታ የገዢዉ ፓርቲ ባለሥልጣናትም እራሳቸዉ የወ/ት ብርቱካንን መታሰር ተቃዉመዋል የሚባል ነገር አለ።  ይህም የሚያሳየዉ እነርሱም እውነት የት እንዳለች ማወቃቸዉን ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን ወደ ወህኒ ከታሰረች ሁለት ወራት አለፉት። በዚህ ሁሉ ጊዜ ሕግ መንግስቱ እንደሚደነግገዉ የሰብዓዊ መብቷ ተረግጦ፣ ዘመድ፣ ጠበቃ፣ ሐኪም እንዳታይ ተከልክላ፣ ሁለት ሜትር በሁለት ሜትር በሚሆንና  ፀሐይ በማያስገባ ጨለማ ቤት እንድትታሰር ተደርጋለች። በማንም ወንድ እሥረኛ ያልተደረገ ግፍ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ እየደረሰ ነዉ። ተሳስቼ ሊሆን ይችላል .... ከሁለት ወር በላይ ጨለማ ቤት የታሰረ ሌላ ሰዉ አላወቅም።

ወ/ት ብርቱካን በቀላሉ የተጠየቀቻዉን አድርጋ ከልጇና ከእናቷ ጋር እንደ ሌሎች ኢትዮጵያዉያን መኖር ትችል ነበር። ነገር ግን «ያልሆነዉን ሆነ» ብሎ መኖር እራስን መሸጥና ባርነት መሆኑን ተገነዘበች። መንፈሷን ማሰር እንደሆነ ተረዳች። «መንፈስ ከሚታሰር ሥጋ ቢታሰር ይሻላል። ሕሊናዬን ፣ ሰዉነቴን ሸጬ ከምኖር መታሰር አይደለም መሞት እመርጣለሁ» አለች።

ዮሴፍ ምንም እንኳን በጊዜዉ የነበሩ ባለሥልጣናት በዉሸትና በእልህ ቢነሱበትም እግዚአብሄር ከርሱ ጋር ነበር። በጊዜዉና በሰዓቱ ከእሥር ቤት ወጣ። ለግብጽ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ተሾመ። ለግብጽ ብቻ ሳይሆን በአካባቢዉ ለሚኖሩ ሕህቦች ሁሉ በረከት ሆነ።

አሁን በአራት ኪሎ ዊስኪ የሚጠጡት ባለሥልጣናት በወ/ት ብርቱካን ላይ ግፍ ጭነዉባታል። «የት ትደርሳለች። ዋጋዋን ነዉ የምናሳያት። የተማመነችባቸዉ እስቲ ሲያስወጧት እናያለን ..»

እያሉ በእልህና በጥላቻ ሊሳሳቁና ሊዘብቱ ይችላሉ። ነገር ግን ያልተረዱትና የታወረባቸዉ ሁለት ቁም ነገሮች አሉ።

የመጀመሪያዉ አንዲቷን ብርቱካን ሚደቅሳ አስረዉ ነገር ያበቃለት መስላቸዉ ነበር። ግን ተሳሳቱ። በአሥር ሚሊዮን የምንቀጠር ብርቱካን ሚደቅሳዎች ተወለድን።

ይሄ ብቻ አይደለም። ከኛም በላይ ደግሞ ለእዉነት የቆመን ከሰማይ ሆኖ የሚመለከት ታላቁ እግዚአብሄር አለ። በርግጥ እግዚአብብሄር ከርሷ ጋር ነዉ። ሰዎች እንዳያናግሯት ብትከለከልም እግዚአብሄር አባቷ ነዉና በመንፈሱ ያናግራታል። ያበረታታል። ያጽናናታል። ለእዉነት፣ ለፍትህ፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሰላም ስትል አሁን እየተሸከመችዉ ያለዉን ግፍ የምትቋቋምበት ኃይልና ጉልበት እግዚአብሄር ይሰጣታል።

ለጊዜዉ የሚስቁ ሊስቁና ሊያሾፉ ይችላሉ። ነገር ግን በጊዜዉና በሰዓቱ ወ/ት ብርቱካን ትፈታለች። ከእሥር ቤት ስትወጣ ደግሞ ዳግማዊት ጥያቱ ብጡል የኢትዮጵያ እናት ሆና ለዘመናት በዘር በኃያማኖት በመደብ ስንከፋፈልና ስንጨራረስ የነበርነዉን በአንድ ላይ ታሰባስባለች።